# በኮሎምቢያ አውራጃ የዞን ክፍፍል ማውጣት

**የዞን ክፍፍል ማውጫ ጽ/ቤት**
**የዞን ክፍፍል ማውጫ ኮሚሽን**
**የዞን ክፍፍል ማውጫ ማሻሻያ ቦርድ**

441 4th Street, NW, Suite 200/210-S
Washington, DC 20001
(202) 727-6311
(202) 727-6072 - ፋክስ
www.dcoz.dc.gov
dcoz@dc.gov



## የዞን ክፍፍል ማውጫ ጽ/ቤት (OZ)

የዞን ክፍፍል ማውጫ ጽ/ቤት (OZ) የዞን ክፍፍል ማውጫ ኮሚሽንና
የዞን ክፍፍል ማውጫ ማሻሽያ ቦርድ የአስተዳደር ክንድ ነው። OZ ለ
ዞን ክፍፍል ለውጥ ወይም የዞን ክፍፍል እንዲቀር የሚቀርቡትን ማመል
ከቻዎችን ይቀበላል፣ ያስፈጽማልም፤ ስብሰባዎችንና ችሎቶችን ይካፈላ
ል እናም ተከታይ የማጠቃለያ ውሳኔዎችን ያቀርባል፤ የዞን ክፍፍል ማ
ውጫ ሂደቶችን ከፕላን ጽ/ቤትና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ያስተባብራ
ል፤ የዞን ክፍፍል ማውጫ ደንቦችን( ጽሑፍና ካርታ) ይጠብቃል ያድሳል
ም፤ የZC እና BZA አባላት ለሚጠይቁት ለተለያዩ ጥያቄዎች ምላሽ ይ
ሰጣል፤ ለፍርድ ጉዳዮች መዝገቦችን ያዘጋጃል፤ ከየዕለቱ የቢሮ ሥራዎ
ች ጋር የተያያዙትን ሁሉንም የአስተዳደር ጉዳዮችን ይይዛል። OZ ስለ
ሕጋዊ ጉዳዮች በተመለከተ ከኮርፖሬሽን ምክር ቤት ጋር ይወያያል እና
ም ስለ ዞን ክፍፍል በተመለከተ ZCና BZA በዞን ክፍፍል ላይ ተፅዕ
ኖ በሚያደርጉት ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ላይ እንዲኖራቸው ዘንድ የአውራ
ጃውን የሕግ ሕደት ይቆጣጠራል። OZ ደግሞ፣ስለ ዞን ክፍፍል ሂደት፣ ስ
ለ ዞን ክፍፍል ደንቦቹ፣የአንድ የተወሰኑ ንብረቶች የዞን ክፍፍል፣ እናም
ከZC ና BZA በፊት ዘግይተው ስላሉት ጉዳዮች በተመለከተ ሕዝባዊ መ
ረጃ ይሰጣል።

### ተልዕኮው

በኮሎምቢያ አውራጃ ለዞን ክፍፍል ኮሚሽንና ለዞን ክፍፍል ቦርድ ማስተ
ካከያ ለዞን ክፍፍል ደንብ ለማውጣትና ለመጠበቅ አስተዳደራዊና የቴክኒ
ክ እገዛ ለማቅረብ

DEPARTMENT OF CONSUMER & REGULATORY AFFAIRS

## በDCRA የዞን ክፍፍል አስተዳዳሪ (ZA) ጽ/ቤት

**የዞን ክፍፍል አስተዳዳሪ በርዕሰ 11 DCMR መሠረት የሚከትሉትንም ጨምሮ ማመልከቻዎች ከዲ ሲ የዞን ክፍፍል ደንቦች ጋር መጣጣማቸውን ለማወቅ ይገመግማል፥**

- ለፈቃድ መስጫ ማዕከል የሚቀርቡ የግንባታ ፈቃድ ማመልከቻዎችን
- ለቦታ ይዞታ ማረጋገጫ (Certificate of Occupancy (C of O) የሚቀርቡ የፈቃድ ማመልከቻዎችን - ለሚፈቀዱ አገልግሎቶች፣ ለ C of O ውሳኔ መስጫ ፍተሻና የግንባታ ፕላን ማስፈለጉን ለማወቅ የይዞታ መጠን፣ አድራሻና ትክክለኛውን ቦታ ማረጋገጥ
- የንዑስ ክፍሎች (Subdivision) ማመልከቻዎች— እነርሱ የቦታውን መጠን፣ ስፋትና ሌሎች መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ

- የቤት ይዞታ (Home Occupation) ፈቃድ ወይም (HOP))–ለ ሚፈቀዱ ነገሮች፣ የሠራተኛና የደንበኛ ጉብኝት ገደቦች፣ እናም ጥቅ ም ላይ ለሚውላው የመኖሪያ ዓይነት ማረጋገጫ የሚቀርቡ ማመልከ ቻዎች

- የዞን ክፍፍል አስተዳዳሪ ልዩ ዓይነት ነገሮችን ወይም ወጥ ያልሆኑ ትን ነገሮች ከፈለገ የአመልካቾችን ማመልካቻዎች እምቢ ብሎ ለዞን ክፍፍል ማስተካከያ ቦርድ ይጽፋል።

የዞን ክፍፍል አስተዳዳሪ ጽ/ቤት ደግሞ የሚከተሉትን አገልግሎቶችን ደግ ሞ ይሰጣል፥

- የዞን ክፍፍል መጣጣሚያ ደብዳቤዎች፣ በአንድ በተወሰነ ንብረት ላይ ስለ ዞን ክፍፍል አካባቢና ስለዞን ክፍፍል ደንቦች መጣጣም በተመለ ከተ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት

- አጠቃላይ የዞን ክፍፍል መረጃ፣ ንብረቱ በየትኛው ዞን ይገኛል የሚለ ውን ጨምሮ


- የንብረቱ የወደፊቱን የተወሰነ የዕድገት ሁኔታ ለማወቅ ለሚፈልጉ አል ሚዎች ወይም የንብረት ባለቤት ለሆኑት ሰዎች የቅድሚያ እቅድ የክ ለሳ ስብሰባዎች(PDRMs) ( ክፍያ ያስፈልጋል)


የዞን ክፍፍል አስተዳዳሪ ጽ/ቤት  
(Office of the Zoning Administrator)  
የተጠቃሚና የድንጋጌ ጉዳዮች  
(Department of Consumer & Regulatory Affairs)  
1100 4th Street, SW  
Washington, DC 20024  
(202) 442-4576  
ሞገደ ማዕከል፥ www.dcra.dc.gov  
ኢ- ሜይል፥ dcra@dc.gov


DCOZ

## የዞን ክፍፍል ኮሚሽን (ZC)


የዞን ክፍፍል ኮሚሽን (ZC)፣ እንደተሻሻለውና የዞን ክፍፍል ደንቦችንና ካርታዎችን ለማዘጋጀት፣ ለመቀበልና ከዚያም ለማስተካከል በ1920 የዞን ክፍፍል አዋጅ መሠረት የተቋቋመ አምስት አባላትን የያዘ የሕግ ነክ ኮሚሽን ነው። ZC ደግሞ የታቀደ የቤት ልማት ጉዳዮችን (Planned Unit Development (PUD) ያዳምጣል -- ፕሮጄክቱ ለሕዝብ በርካታ መጠን ወይም ጥራት ያላቸውን ጥቅሞችን የሚያበረክት ከሆነና የሕዝብ ጤናን፣ ዳህንነት፣ በጎነትና ምቾት የሚያስፋፋ ከሆነ ለአልሚው ትልቅ ቅልጥፍናና ሌሎች ጥቅሞችን የሚፈቅድ የታቀደ መሣሪያ ነው። የZC ሦሥት አባላት በካንቲባው የተሾሙና በምክር ቤቱ የፀደቁ የኮሎምቢያ አውራጃ ኗሪዎች ናቸው፤ አረተኛው አባል የዋና ከተማው አርክቴክት- AOC ( ወይም የርሱ/የርሷ ተወካይ) ነው፤አምስተኛው የብሔራዊ መናፈሻ አገልግሎት- NPS ( ወይም የርሱ/የርሷ ተወካይ) ነው።






## የዞን ክፍፍል ማሻሸያ ቦርድ (BZA)

የዞን ክፍፍል ማሻሸያ ቦርድ (BZA) እንደተሻሻለውና ከልዩ ጉዳዮች፣ ለየት ካሉ ሁኔታዎችና፣ የአስተዳደር ውሳኔዎች ጋር በተያያዘ አቤቱታዎችን ለማዳመጥ ኃላፊነት የተሰጣው በ1938 የዞን ማስቻያ አዋጅ  መሠረት የተቋቋመ አምስት አባላትን የያዘ የሕግ ነክ ቦርድ ነው።
BZA ደግሞ  የውጭ ተልዕኮ ጉዳዮችንና ሲቪል መጣስና ያዳምጣል። የBZA ሦሥት አባላት በካንቲባው የተሾሙና በምክር ቤቱ የፀደቁ የኮሎምቢያ አውራጃ ዷሪዎች ናቸው፤ አንዱ የብሔራዊ ካፒታል ፕላኒንግ  ኮሚሽን (NCPC)  አባል ወይም ባልደረባው ነው፤እናም አንዱ የZC አባል ነው።






## የDCOZ መገናኛ መረጃ

Richard Nero, Jr.
የድርጊቶች ምክትል ሥራ አስኪያጅ
(202) 727-2806
richard.nero@dc.gov

Nyambi A. Nyambi, AICP
ዋና የቴክኖሎጂ መኮንን
(202) 727-0314
nyambi.nyambi@dc.gov

Sharon Schellin
የዞን ክፍፍል ኮሚሽን ጸሐፊ
(202) 727-0340
sharon.schellin@dc.gov

Cliff Moy
የዞን ክፍፍል ማሻሻያ ቦርድ ጸሐፊ
(202) 727-0348
clifford.moy@dc.gov

Tracey Rose
የትዕዛዝ ክለሳ መርኃ ግብር ሥራ አስኪያጅ
(202) 727-0349
tracey.rose@dc.gov

Sara Bardin
ልዩ ረዳት/የሕዝብ መረጃ/
የቋንቋ ማቅረቢያ አስተባባሪ
(202) 727-5372
sara.bardin@dc.gov